# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ታህሳስ 20 ቀን 2005 ዓ.ም**

**የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቲ ድንገተኛና አስቸኳዋይ ስብሰባ አደረገ፤**

**በአዲግራት ከተማ የተቀሰቀሰው የሙስሊሙ ህዝብ ተቃውሞ አሁንም እንደቀጠለ ነው፤**

**ጦሩ በያለበት በተጠንቀቅ እንዲቆም መታዘዙ ተጋለጠ፤**

**በሰራዊቱ ውስጥ ያለውን ችግር ለመሸፈን ሲባል የመከላከያ ቀን በሚል በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ ተደረገ፤**

**የወያኔ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቲ አባላት ቅዳሜ ታህሳስ 13 እና ዕሁድ ታህሳስ 14 ቀን 2005 ዓ.ም ለሁለት ተከታታይ ቀናት በጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ አስቸኩዋይ ስብሰባ አደረገ፡፡**

**የእርስ በርስ ሽኩቻቸውን ለግዜው ወደ ጎን በመተው የህዝቡን ድጋፍ ለማግኘት እና መጪውን ምርጫ ለማዘጋጀት ሲሉ በአሁኑ ሰዓት ከመቼውም ግዜ በላይ በመላ ሀገሪቱ የዋጋ ግሽበቱ እየጦዘ ባለበት ሰዓት ግሽበቱ ቀንሶዋል....የኑሮ ውድነቱ ጣራ እየነካ መሆኑን**

ክደው ተትረፍርፎዋል.....እያሉ ሰፊ ሽፋን ለመስጠት እንዲያመቻቸው ህዝቡን በውሸት ፕሮፓጋንዳ ለማታለል ያደረጉት ስብሰባ መሆኑንም ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

የዋጋ ግሽበቱ ከ39 በመቶ በላይ ንሮ ባለበት በዚህ ግዜ በሀገሪቱ ያለውን ነባራዊ እውነታ ክደው በህዳር ወር ወደ 15.6 በመቶ ግሽበቱ አሽቆልቁሎዋል በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ደግሞ ወደ ነጠላ አሀዝ እንዲወርድ ተግተን እየሰራን ነው በማለት ሕዝቡን በተቆጣጠሩት ቲሌቪዥን እና ራዲዮ ለማሰልቸት አዲስ ፕሮፓጋንዳ ሊነዙ መሆኑንም ከዜና ምንጮቻችን ያገኘነው ዜና ይጠቁማል፡፡

የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ለማክበር በሚል በባህር ዳር ለተደረገው ዝግጅት ከ5 ቢሊዮን ብር በላይ ተበትኖ......የባንዲራ ቀን በሚል በመላ ሀገሪቱ ለፕሮፓጋንዳና ለወያኔ ካድሬዎች እና የፎረም አባላት አበል ተብሎ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር እየናዱት ......በየባንኮቹ ውስጥ ብር ጠፍቶ በመላ ሀገሪቱ ስራ ቆሞ እያለ ዛሬ በሀገሪቱ ታይቶ የማይታወቅ እድገት እየተመዘገበ ነው እያሉ እራሳቸውን ጭምር እያታለሉና እያጃጃሉ ያሉት የወያኔ ቁንጮ ባለስልጣናት በራሳቸው ጉዳይ የተከሰተውን ችግር ለማዳፈንና ጨርሶ ህዝቡ እንዳያውቀው ለማድረግ ታስቦ አስቸኩዋይ ስብሰባው ሊደረግ እንደቻለ ምንጮቹ ተናግረዋል፡፡

በቢሊዮን የሚቆጠር ብር በጀት ተመድቦለት እና ሙሉ ገንዘቡ ወጪ ተደርጎ የት እንደገባ ያልታወቀበት የሶስት ስኩዋር ፋብሪካ ግንባታ ሂደት..... የመብራት ኃይል አቅርቦት በእጅጉ አሳሳቢ የሆነበት ደረጃ ላይ መድረሱ......በየግዜው በተለያዩ ምክንያቶች ከስልጣናቸው ስለሚነሱ ባለስልጣናት የወደፊቱ እጣ ፈንታ.....በቀጣይ መወሰድ ስላለበት የድርጅቱ እርምጃ ላይ ውይይት ለማድረግ በተለያዩ የስራ አስፈጻሚዎች የተነሳ ሀሳብ የነበረ ቢሆንም እርስ በርስ ሳይተማመኑና ሳይግባቡ በመቅረታቸው ለተነሱት ሀሳቦች አጣሪ ኮሚቴ ተሰይሞ እንዲያቀርብ በሚለው ላይ ብቻ ተስማምተው መለያየታቸው አሁንም በወያኔ ውስጥ ያለው ችግር አስቸጋሪ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያስረዳል ብሎዋል፡፡

በተለይ ከቅርብ ግዜ ወዲህ የወያኔን ገመና የሚያወቁ ባለስልጣናት ከስልጣናቸው ሲነሱ በስራ ላይ በቆዩባቸው ዓመታት ለድርጅቱ ለዋሉት ውለታ ምን ሊደረግላቸው ይገባል ይህ ካልሆነ ግን ለሚከሰተው ችግርስ ተጠያቂው ማነው በሚለው ላይ ከኦህዴድ ስራ አስጻሚዎች አንዱ ጥያቄ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ድርጅቱን ሲሽረሽሩ እና ሲቦረቡሩ ለነበሩት ሰዎች ወይም ድርጅቱን ለአደጋ ሊዳርጉ ለነበሩ ሰዎች የተለየ እንክብካቤ እና ድጋፍ ይደረግላቸው ብሎ ሀሳብ ማቅረቡ የጤነኛ ሰው አስተሳሰብ ካለመሆኑም በተጨማሪ በድርጅቱ ላይ ጦር እነደመስበቅ ይቆጠራል በሚል አንዳንድ የህወሀት ስራ አስፈጻሚ አባላት ተረባርበው ቁጣ አዘል መልስ በመስጠታቸው ጥያቄው ሳይመለስ ተዳፍኖ መታለፉንም ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በዚሁ በተደረገው አስቸኩዋይ ስብሰባ ወቅት አንድ ቀን ተኩሉን በይፋ ተቀርጾ የተሰበሰቡ ሲሆን ግማሽ ቀንዋ ግን በዝግ ብቻቸውን በማድረጋቸው የተላለፈውን እና በምስጢር ያደረጉትን ጉዳይ ለማወቅ እንዳልተቻለም ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

በሌላ ዜና በአዲግራት ከተማ የተቀሰቀሰው የሙስሊሙ ህዝብ ተቃውሞ በመስፋፋቱ ለወያኔ ቡድን ተጨማሪ  የእራስ ምታት እና የውስጥ እግር እሳት እንደሆነበት ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

ከአዲግራት ወደ ዛላንበሳ በሚወስደው መንገድ የአዲግራት ከተማ የእስልምና መካነ መቃብር በመፍረሱ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ተቃውሞ መቀስቀሱን ተከትሎ በወያኔ ቡድን ውስጥ ከፍተኛ ትርምስ እየተፈጠረ እንደሚገኝ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

መንገዱ የመካነ መቃብሩን ስፍራ ሳይነካ መሰራት እንደሚችልና ከበቂ በላይ ቦታ እንዳለው የገለጹት የአዲግራት ከተማ ነዋሪዎች በአሁኑ ሰዓት በመላ ሀገሪቱ የተነሳውን የሙስሊሙ ህዝብ ቁጣ ለማባባስ በሚመስል መልኩ እዚህም ተመሳሳይ እርምጃ መወሰዱ የሚያሳዝን እና ወያኔ የውስጥ ችግሮቹን መሸፈኛ ለማድረግ ነው ይላሉ::

የወያኔ ባለስልጣናት ስልጣናቸውን መከታ በማድረግ ተከብሮ የኖረውን የሙስሊሙ መቃብርን ካልጠፋ ቦታ ቁርዓናችን በማያዝዘው መልኩ... ሳይነገረንና ሳናውቀው .....ሀሳባችንን እንኳዋን ሳንሰጥ እና ሳንጠየቅ እንዲፈርስ መደረጉ ሙስሊሙን ህዝብ መናቃቸውን ያሳየ ነው ያሉት አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ሙስሊም አባት ተቃወሙ የተባሉትን የእምነቱ ሰዎች ቤት ለቤት እያሰሱ ለእስራት መዳረጋቸው የሚያሳዝን እና የሚያበሳጭ ነው ብለዋል::

ላለፉት አንድ ዓመት የጥፋት ሀሳባቸውን በግልፅ ሳይናገሩ በስውር ብቻ ሙስሊሙን እያስፈራሩና እያዋከቡ ሲያንገላቱት የቆዩት የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት  አሁን ሙስሊሙን ለማበሳጨት ሲሉ ባልጠፋ ቦታ የሙስሊሙን መቃብር እንዲፈርስ ማድረጋቸው ሙስሊም የሆነ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በሀገሪቱ ውስጥ መኖር የለበትም የሚል አቋዋም የያዙ ያስመስላቸዋል ሲሉም እኚሁ የአዲግራት ነዋሪ የሙስሊም አባት በንዴት ሲገልጹ ተደምጠዋል::

የአዲግራት የእስልምና አስተዳዳሪ የሆኑት  ሼህ ሁሴንን የጸጥታ ኃይሎች አንዴ ከሌሊቱ 6 ሰዓት...ሌላ ግዜ ከመንገድ ላይ አፍነው......እንዲያም ሲል ከቢሮዋቸው  እየወሰዱዋቸው.... እያዋከቡዋቸው ከመሆኑም በላይ በጾም በጸሎት ግዜ ድንገት መስጊዱን በፌዴራል ፖሊስ እና በልዩ ኃይል እያስከበቡ ሲያስፈራሩን መሰንበታቸው አንሶ አሁን ደግሞ ለብዙ ዘመናት ተከብሮ የኖረውን የሙስሊሙን መቃብር በአንድ ሳምንት እንዲፈርስ ማድረጋቸው አስገራሚ እና አስደንጋጭ ነው ሲሉም እኚሁ አባት ተናግረዋል::

የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ከዚህ ቀደም እንደሚያደርጉት ሁሉ አሁንም የአዲግራት ነዋሪ የሆነውን ሙስሊም ብጥብጥ አነሳ ብለው ፕሮፓጋንዳ ሊሰሩበት ተዘጋጅተው የመጡ ቢሆንም ህዝበ ሙስሊሙ ግን ቀድሞ በማወቁ በትዕግስት እና በጨዋነት ምላሽ በመስጠቱ የተበሳጨት ባለስልጣናቱ የቀብር ቦታውን በዶዘር ማፍረሳቸውን ተናግረዋል::

በአሁኑ ሰዓት በግሬደር እና በዶዘር እየፈረሰ የሚገኘው የአዲግራት የሙስሊሙ መቃብር ቦታ ከ70 በመቶ በላይ የአፋር መስሊሞች የተቀበሩበት መሆኑን  ከስፍራው የደረሰን ዜና የጠቆመ ሲሆን

ጉዳዩን የአፋር ተወላጆች እንዳልሰሙና ይህን ድርጊት ቢያውቁ የከፋ አደጋ ሊፈጠር ይችላል ሲል ዜናው ይገልጻል::

በአዲግራት ከተማ ቀበሌ 01 ተብሎ በሚጠራው ሰፈር የሚገኘው መስጊድ ውስጥ ህዝበ ሙስሊሙ በመገኘት የደረሰባቸውን በደል በጸሎት እንዳይገልጹ በመከልከላቸው በየሰፈራቸው ለመስገድ እንደተገደዱ ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ የተፈጠረውንና እየሰፋ ያለውን ውጥረት ለማርገብ ሲባል የመከላከያ ቀን በሚል በቅርቡ በመላ ሀገሪቱ በከፍተኛ ድግስ ሊያከብሩላቸው መሆኑ መከላከያ ውስጥ የሚገኙ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል::

ከ1.2 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጎ ከየካቲት 1 ቀን እስከ የካቲት 7 ቀን 2005 ዓ.ም ለሰባት ተከታታይ ቀናት በመላ ሀገሪቱ በተለያዩ ወታደራዊ ዝግጅቶች እንደሚከበር የጠቆሙት ምንጮቹ በአሁኑ ሰዓት ይህን ከፍተኛ ወጭ መድበው በኣሉን ለማከበር የተገደዱበት ምክንያት በሰራዊቱ ውስጥ ያለውን ውጥረት እና ትኩሳት ለማርገብ መሆኑ ታውቋል::

ሰራዊቱ በተደጋጋሚ ግዜ የሚያቀርበውን የመብት ጥያቄ መልስ ባለመስጠታቸው ከበረሀ በመጡት የቀድሞ ታጋይ የአሁኖቹ ጄኔራል መኮንኖች ላይ ቂም ቁዋጥሮ ግዜ እየጠበቀ መሆኑን የተረዱት መኮንኖቹ የሰራዊት አባላቱን ለመሸንገል ከሚጠቀሙበት ዘዴዎች መከከል ይህ አንዱ መሆኑ ነው::

በአሁኑ ሰዓት በልዩነት ተወጥሮ እየጦዘ ያለው የመከላከያ ተቋዋም የተማሩና ወጣት መኮንኖች እና የበታች ሹሞች ከበድ ከበድ ያሉና ለመልስ አዳጋች የሆኑ ጥያቄዎች በመጠየቃቸው ከየክፍላቸው እየተለቀሙና ታፍነው እየተወሰዱ ካልሆነም ደግሞ በተቃዋሚ ፓርቲ አባልነት እየወነጀሉ ለእስር እየተዳረጉ መሆናቸውንና አሁንም ቢሆን ችግሩ እየተባባሰ እንጂ እንዳልተቀረፈ ምንጮቹ አስረድተዋል::

በቅርቡ ከደብረዘይት የአየር ኃይል ዋና ማዘዣ እና ከተለያዩ የጦር መሳሪያ ማምረቻ ፋብሪካዎች ውስጥ ሲሰሩ የነበሩ ወታደራዊ መሀንዲሶች በጦር ኃይሎች መኮንኖች አጠገብ በሚገኝ አስር ቤት ታጉረው እንደሚገኙ፤ እንዲሁም ቁጥራቸው የበዙ ወጣት መኮንኖች ደግሞ የደረሱበት እንዳልታወቀ የምንጮቹ ጥቆማ አብራርቶዋል::

በቅርቡ የመከላከያ ቀን በሚል ሊደረግ የታቀደው ወታደራዊ ትርዒት የወያኔ ቡድን መለስ ከሞተ በሁዋላ ተጠናክረናል ብሎ ሃይሉን ጠላት ለሚላቸው ወገኖች ለማሳየት እና ለማስፈራራት ነው በማለት አንዳንድ የቀድሞ የጦር መኮንኖች ይናገራሉ:::

ግብፅ እና ሱዳን በምስጢር ባደረጉት ወታደራዊ ስምምነት የግብጽ የጦር ጄቶች በግዛትዋ እንዲሰፍሩ ማድረግዋን ተከትሎ የወያኔ ቡድን ከውጭ ሀገር የጦር አማካሪዎችን አስገብቶ በመስራት ላይ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በስድስት ወር ውስጥ ብቻ በተለያዩ የጦር ማሰልጠኛ ካምፖች ከ30 ሺህ በላይ ኮማንዶ ፤አየር ወለድና ልዩ ኃይል ማስረቁን ጨምረው ገልፀዋል::

በዚህም የተነሳ በሀገሪቱ ያሉት ወታደራዊ የጦር ክፍሎች በሙሉ በያሉበት ወታደራዊ ትምህርት እየተሰጣቸው ሲሆን በተለይ በሁርሶ ኮማንዶ ማሰልጠኛ ጦር ካምፕ ውስጥ አሰልጣኝ ሆነው የሚሰሩት የውጭ ሀገር ዜጎች እንደሆኑም ከምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

የማዕከላዊ እዝ በሌ/ጄ/ል አበባው ታደሰ መሪነት መቀመጫውን ሽሬ እንደ ስላሴ አድርጎ ለጦሩ አባላት ስልጠናውን እያከናወነ ከመሆኑም በተጨማሪ ወያኔ ከሻእቢያ ጋር በገባው ውጥረት የተነሳ ጦሩ በዙሪያ ጥበቃ ላይ የሚገኝ ሲሆን የሰሜን እዝ በበኩሉ በሌ/ጄ/ል ሳዓረ መኮንን እየተመራ ስልጠናውን እያከናወነ ከመሆኑም በላይ ጦሩ ለተወርዋሪነት ዝግጁ እንዲሆን መደረጉንም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል፡፡

የምዕራብ ዕዝ በሜ/ጄ/ል ብርሀኑ ዱላ መሪነት አስቀድሞ ስልጠናውን ያጠናቀቀ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በአባይ ግድብ ግንባታ ዙሪያና በሱዳን ድንበር ላይ የተጠናከረ ጥበቃ እያከናወነ ከመሆኑም በተጨማሪ በአየር ኃይል እየታገዘ የአየር ቅኝት በየቀኑ እያከናወነ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

በሜ/ጄ/ል አብርሀ ወ/ማርያም እየተመራ የሚገኘው የምስራቅ እዝ በበኩሉ በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍል በተለይ በኦጋዴን ውስጥ በተነሳ ግጭት በውጥረት ላይ የሚገኝ በመሆኑ በየቀኑ ግጭት እና ቁርቁዋሶ ላይ ያለ የጦር ክፍል መሆኑንም ምንጮቹ ጨምረው አጋልጠዋል፡፡

በቅርቡ ይከበራል በተባለው የመከላከያ ቀን በቢሊዮን ብር የሚረጭበት በዓል ላይ በመላ ሀገሪቱ ያሉ የሰራዊቱ አባላት ይሳተፋሉ ተብሎ የሚጠበቅ ቢሆንም በሱማሌና በኦጋዴን ለረገፉት የሰራዊቱ አባላት ማስታወሻ የሚሆን አንድም ሐውልት ሳይቆምላቸው ዛሬም በረሀ በትግል ላይ ሞቱ ለተባሉት የህወሀት ታጋዮች ብቻ መታሰቢያ የሚሆን መዘጋጀቱ በጦሩ ውስጥ የነበረውን ውጥረት ይበልጥ እንደሚያጦዘው ምንጮቹ ስጋታቸውን ገልጸዋል፡፡

በአሜሪካን ፕሬዝዳንት በነበረው በጆርጅ ቡሽ እና በእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር በነበረው ቶኒ ብሌየር ትዕዛዝ እና አይዞህ ባይነት ከኢትዮጵያ ህዝብ እውቅናና ይሁንታ ውጭ ሙዋቹ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ጦሩን ሱማሊያ አስገብቶ ያስጨረሰው ከመሆኑም ባሻገር አስከሬናቸው እንደ አልባሌ በየመንገዱ ላይ እየተጎተተ እና ቀባሪ አጥቶ የነበረ መሆኑን አስታውሰው በዛን ወቅት ለሞቱት እና አሁንም እየሞቱ ላሉት የሰራዊቱ አባላት ቤተሰብ አንዳችም ድጋፍ ሳይደረግ ይባስ ብለው መርዶ እንኩዋን እንዳይነገራቸው ተብሎ ተዳፍኖ መገኘቱ ሳያንስ ማስታወሻ ሐውልት አለመሰራቱ በጦሩ ውስጥ ያለውን ክፍፍል አጉልቶ ያሳያል ሲሉ ምንጮቹ ይገልጻሉ፡፡